መልእክት አሥራ-ሁለት

## የከንቱ ከንቱ፣ በኢየሱስ ያለው እውነታ፣
## እና የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፡- መክ. 1፡2-11፣ 14፤ 2፡17፣ 22፤ 3፡11፤ 12፡8፤
መዝ. 39፡4-6፤ ኤፌ. 4፡17-21፣ 24፤ 1 ዮሐ. 5፡20፤ ሮሜ 8፡19-22

**I. "የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው"—መክ. 1፡2፡-**

ሀ. በመጽሐፈ መክብብ 1፡2-11 የዚህ መጽሐፍ ጭብጥ የከንቱ ከንቱ መሆኑን እናያለን፡-

1. የመጽሐፈ መክብብ ማዕከላዊ ሃሳብ ከእግዚአብሔር ተለይቶ በመውደቁ ከፀሐይ በታች የሰው ሕይወት የከንቱ ከንቱ መሆኑ ነው—ቁ. 2።
2. የመጽሐፈ መክብብ ይዘቶች ከፀሐይ በታች ስለወደቀው ሰው የስብዕና ሕይወት፣ በተበላሸው ዓለም ውስጥ ስላለው ሕይወት መግለጫ ናቸው—ኤፌ. 2፡12።
3. በመጽሐፈ መክብብ ውስጥ ያሉት የሰሎሞን ትምህርቶች በተበላሸው ዓለም ውስጥ ያለው የሰው ሕይወት ከንቱ፣ ነፋስን እንደመከተል እንደሆነ ያሳያሉ—1፡14።
4. በመጽሐፈ መክብብ መሠረት፣ የስብዕና ታሪክ ከጅማሬው አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ ከንቱ ነው—12፡8።
5. አንድ ነገር ምንም ያህል መልካም፣ የላቀ፣ እጹብ እና ድንቅ ቢሆንም፣ ከአሮጌው ፍጥረት እስከሆነ ድረስ ከፀሐይ በታች ያለ የከንቱ ከንቱ ክፍል ነው—1፡9፤ 2፡11፣ 17፣ 22።
6. "ከፀሐይ በታች" (1፡9) ያለው ሳይሆን በሰማያት ያለው አዲሱ ፍጥረት ብቻ ከንቱ አይደለም ነገር ግን እውነታ ነው—2 ቆሮ. 5፡17፤ ገላ. 6፡15፤ ኤፌ. 4፡24።

ለ. በመዝሙር 39፡4-6 ዳዊት የሕይወቱን ምንምነት እና ከንቱነት ተገነዘበ፡-

1. በዚህ መዝሙር ውስጥ ዳዊት ምንም እና ከንቱ መሆኑን በእግዚአብሔር እንዲገነዘብ ተደረገ፤ ምርጥ በተባለው ሁኔታው ሆነ ደረጃው እያንዳንዱ ሰው ሙሉ በሙሉ ከንቱ እንደሆነ ተማረ—ቁ. 5።
2. ሁናቴያችን ኃጢአተኛ (መዝ. 38) እንደሆነ እና ሁኔታችን ከንቱ እንደሆነ መገንዘባችን በገላትያ 2፡20 በጳውሎስ እንደተገለጠው ራሱን በእኛ በኩል በመኖር እና በሕይወታዊ ጥምረት ውስጥ ከእርሱ ጋር በአንድ ላይ እንድንኖር በማድረግ ክርስቶስ ይሰቀለን ዘንድ እና እኛን ለመተካት ወደ ውስጣችን ይገባ ዘንድ መንገድ ይከፍትለታል።

ሐ. ሰው በእግዚአብሔር የተፈጠረው በከፍተኛ እና እጅግ በከበረ አላማ፣ ያውም፣ ከመለኮታዊ ሕይወቱ እና ባሕሪው ጋር እግዚአብሔርን በመልኩ ለመግለጥ ነበር—ዘፍ. 1፡26፡-

1. የእግዚአብሔር ጠላት፣ ሰይጣን፣ ዲያቢሎስ፣ ለአላማው በእግዚአብሔር ወደተፈጠረው ሰው ውስጥ ራሱን እንደ ኃጢአት ለማስገባት መጣ—3፡1-6፤ ሮሜ 5፡18፤ 3፡23፤ 1 ዮሐ. 3፡4።
2. በዚህ የሰው ውድቀት በኩል፣ ሰው እና ለመግዛቱ በእግዚአብሔር የተሰጡት የተፈጠሩ ነገሮች በሙሉ ለከንቱነት ተገዙ (ሮሜ 8፡20-21)፤ በመሆኑም፣ በተበላሸው ዓለም ውስጥ ያለው የሰው ሕይወትም ከንቱ ሆነ።
3. ከዚህ ከንቱነት የምናመልጥበት መንገድ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ መምጣት እና እግዚአብሔርን በክርስቶስ እንደ ቤዛነት፣ ሕይወት፣ ሀብት፣ ድሰታ፣ ደስታ እና እርካታ መውሰድ ነው ይኸውም ለዘላለማዊው ኢኮኖሚው መፈጸም ሰውን በመፍጠሩ ያለውን የመጀመሪያ አላማውን ለመፈጸም አሁንም በእግዚአብሔር ጥቅም ላይ እንውል ዘንድ ነው—መክ. 12፡13-14።

መ. በተበላሸው ዓለም ውስጥ ያለው የሰው ሕይወት ከንቱ፣ ነፋስን መከተል ቢሆንም፣ እግዚአብሔር በሰው ልብ ውስጥ ዘላለምነትን እንዳስቀመጠ መገንዘብ ያስፈልገናል—3፡11፡-

1. በመጽሐፈ መክብብ 3፡11 ያለው "ዘላለምነት" "በዘመናት ሁሉ የሚሠራ በመለኮታዊ መንገድ የተተከለ ተጨባጭ የሆነ የአላማ ግንዛቤ" ነው (ዘ አምፕሊፋይድ ባይብል)።
2. እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረው በውስጡም መንፈስን ሠራ ይኸውም እግዚአብሔር የሰው እርካታ መሆን ይችል ዘንድ ሰው እንዲቀበለው እና እንዲይዘው እግዚአብሔር ራሱን የሚሻ ልብ እንዲኖረው ነው—ዘፍ. 1፡26፤ ዘካ. 12፡1።
3. ሰው ከእግዚአብሔር ተለይቶ ቢወድቅም፣ እንዲሁም ለእርካታው እግዚአብሔርን ከመቀበል ሰውን ለማስተጓጎል ኃጢአት በሰይጣን በኩል ቢመጣም፣ እግዚአብሔርን መሻት፣ እግዚአብሔርን መፈለግ አሁንም በሰው ልብ ውስጥ ቀርቷል—መክ. 3፡11።

4. ጊዜአዊ ነገሮች ሰውን ፈጽሞ ሊያረኩት አይችሉም፤ ዘላለማዊው አምላክ ብቻ፣ እርሱም ክርስቶስ፣ በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ጥልቅ ተጨባጭ የአላማ ግንዛቤ ማርካት ይችላል—ተዛ. 2 ቆሮ. 4፡18።

**II. በኤፌሶን 4፡17-21 እና 24 ከእንግዲህ ወዲህ በአእምሮ ከንቱነት ላልሆነ ምልልስ ጳውሎስ በኢየሱስ ያለውን እውነታ ያቀርባል፡-**

ሀ. በኤፌሶን 4፡17 ጳውሎስ "አሕዛብ ደግሞ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ [እንዳይመላለሱ]" አማኞችን ይመክራል፡-

1. በወደቀው ሰው የየዕለት ሕይወት ውስጥ ያለ መሠረታዊው ንጥረ-ነገር የአእምሮ ከንቱነት ነው።
2. አሕዛብ በሃሳባቸው ከንቱ የሆኑ የወደቁ ሰዎች ናቸው—ሮሜ 1፡21፡-
   ሀ. ያለ እግዚአብሔር በአእምሮአቸው ከንቱነት ይመላለሳሉ በከንቱ አስተሳሰቦቻቸውም ቁጥጥር ሥር የሆኑና የሚመሩ ናቸው።
   ለ. በእግዚአብሔር እና በሐዋርያው ጳውሎስ ዓይኖች፣ በዓለም ያሉ ሰዎች የሚያስቡት፣ የሚናገሩት እና የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ሌላ ነገር ሳይሆን ከንቱነት ነው።
3. በአእምሮአቸው ከንቱነት የሚመላለሱት አሕዛብ በልባቸው ደንዳናነት ጠንቅ ልቡናቸው ጨለመ—ኤፌ. 4፡18፡-
   ሀ. የወደቁ ሰዎች አእምሮ በከንቱነት ሲሞላ፣ የእግዚአብሔርን ነገሮች በተመለከተ ልቡናቸው ጨለመ—መዝ. 94፡11።
   ለ. የወደቀው ሰው ልብ ደንዳናነት በልቡናው ያለው ጨለማ እና የአእምሮው ከንቱነት ምንጭ ነው—ኤፌ. 4፡17-18።

ለ. በኤፌሶን 4፡17 እና 21 በኢየሱስ ባለው እውነታ እና በወደቀው የሰው አእምሮ መካከል ንጽጽር አለ፡-

1. በወደቀው ሰው እግዚአብሔር-የለሽ ምልልስ ውስጥ ከንቱነት አለ፣ ነገር ግን በኢየሱስ እግዚአብሔራዊ (godly) ሕይወት ውስጥ እውነታ አለ።
2. በኢየሱስ ያለው እውነታ በቁጥር 24 የተጠቀሰው የአዲሱ ሰው "እውነታ" ነው፡-
   ሀ. ሚያታልለው (ቁ. 22) የሰይጣን አካል መልበስ (መልከ ምሳሌ) ነው፣ እውነታው (ቁ. 24) የእግዚአብሔር አካል መልበስ ነው፤ ሚያታልለው ዲያቢሎስ ነው፣ እውነታ ደግሞ እግዚአብሔር ነው።
   ለ. እግዚአብሔር እንደ እውነታ በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ ታይቷል—ቁ. 21።
3. በኢየሱስ ያለው እውነታ በአራቱ ወንጌላት የተዘገቡት የኢየሱስ ሕይወት እውነተኛ ሁኔታ ነው፡-
   ሀ. የኢየሱስ የስብዕና ኑሮ በእውነታ መሠረት፣ ማለትም፣ በእግዚአብሔር በራሱ መሥረት ነበር—ኤፌ. 4፡24።
   ለ. የኢየሱስ ሕይወት ውስጠ-ነገር እውነታ ነበር፤ እርሱ ሁልጊዜ በእውነታ ተመላለሰ።
   ሐ. ጌታ በስብዕና ሕይወቱ ያደረገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር የተገለጠበት ነበር ስለዚህም እውነታ ነበር።
4. በእውነታ መሠረት የሆነው የኢየሱስ ሕይወት ለአማኞች ሕይወት ምሳሌ ነው—2 ዮሐ. 1-2፣ 4፤ 3 ዮሐ. 3-4፡-
   ሀ. የእውነታን ሕይወት ለመኖር ክርስቶስን መማር እና በእርሱ የተማርን መሆን ያስፈልገናል—ኤፌ. 4፡20-21፤ 2 ዮሐ. 1፤ ዮሐ. 4፡23-24።
   ለ. እንደ የክርስቶስ አካል ብልቶች፣ እውነታ በኢየሱስ እንዳለ የእውነታን ሕይወት—እግዚአብሔርን የመግለጥ ሕይወት—መኖር አለብን።

ሐ. በኢየሱስ ባለው በእውነታ መኖር እንችላለን ምክንያቱም "እውነተኛ በሆነው በእርሱ አለን"—1 ዮሐ. 5፡20፡-

1. *እውነተኛ [የሆነው] እርሱ* የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለእኛ ውስጠ-ልምምዳዊ መሆኑን፣ ውጫዊ የሆነው እግዚአብሔር በሕይወታችን እና በልምምዳችን እውነተኛ የሆነው እርሱ መሆኑን ነው።
2. ጌታ ኢየሱስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ እውነተኛ አምላክ ስለሆነ፣ እውነተኛ በሆነው በእርሱ—በእውነተኛው—መሆን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ መሆን ነው—ቁ. 20።
3. እውነተኛ የሆነው እርሱ መለኮታዊው እውነታ ነው፤ እውነተኛ የሆነውን ማወቅ ማለት ይህን እውነታ በመለማመድ፣ በመደሰት እና የራስ በማድረግ መለኮታዊውን እውነታ ማወቅ ማለት ነው።

**III. ፍጥረት ለከንቱነት ስለተገዛ፣ "ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ" [በሚል] ተስፋ ፍጥረት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በጉጉት ይጠባበቃል—ሮሜ 8፡19-22፡-**

ሀ. ሰይጣን ራሱን እንደ ኃጢአት ወደ ሰው ውስጥ በማስገባቱ፣ ሰው እና የተፈጠሩ ነገሮች ሁሉ ወደ ጥፋት ባርነት ውስጥ መጥተዋል ለከንቱነትም ተገዝተዋል—5፡12፤ 8፡20፡-

1. ፍጥረት ለከንቱነት እና ለጥፋት ባርነት ስለተገዛ፣ ከፀሐይ በታች ያለ ነገር ሁሉ ከንቱ ነው—መክ. 1፡2፤ 12፡8።

2. አሁን ፍጥረት ከመበስበስ እና ከመበላሸት (ከጥፋት) ሕግ ሥር ባርያ ተደርጓል፤ ብቸኛው ተስፋው የእግዚአብሔር ልጆች ሲገለጡ ከጥፋት ባርነት ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት ነፃ መውጣት ነው—ሮሜ 8፡20-21።

ለ. የፍጥረት ናፍቆት—በሙሉ ትኩረት ነቅቶ ማየት—"የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃል"—ቁ. 19፡-

1. መገለጥ ከዚህ ቀደም ተጋርዶ ወይም ተሰውሮ የነበረ ነገር መጋረጃ መነሣት ወይም መገለጥ ነው—ኤፌ. 1፡17፤ 3፡5፤ ገላ. 1፡15-16፤ ራእ. 1፡1።
2. በጌታ ሁለተኛ መምጣት ጊዜ፣ በምንከብርበት እና ሥጋችን ሙሉ በሙሉ በሚዋጅበት ጊዜ፣ መጋረጃው ይነሣል—ሮሜ 8፡18።
3. "እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ" (ቁ. 22) ያለው ፍጥረት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ እየተጠባበቀ ነው (ቁ. 19)።
4. ይህ መገለጥ አሁን እያለፍንበት ያለው የመሰየም ሂደት መጠናቀቅ ነው—ተዛ. 1፡4፣ የግርጌ ማስታወሻ 1።

ሐ. ምንም እንኳ መላው ፍጥረት በአሁኑ ወቅት በከንቱነት እና በመበላሸት ሁኔታ ውስጥ ተይዞ ያለ ቢሆንም፣ የአሁኑን ሁኔታ ለማስወገድ እግዚአብሔር መንግሥቱን ያመጣል—ራእ. 11፡5፡-

1. የሚመጣው መንግሥት የእግዚአብሔር ክብር መንግሥት፣ በዋናነት ከተገለጡ የእግዚአብሔር ልጆች የተዋቀረ መንግሥት ይሆናል—ማቴ. 6፡10፣ 13፤ ሮሜ 8፡19።
2. የእግዚአብሔር ክብር ከመንግሥቱ ጋር አብሮ ይሄዳል በመንግሥቱ ክልል ውስጥም ይገለጣል—ማቴ. 6፡10፣ 13፤ መዝ. 145፡11-13።
3. እግዚአብሔር ወደ መንግሥቱ እና ክብሩ ውስጥ እንድንገባ ጠርቶናል—1 ተሰ. 2፡12፡-
   ሀ. የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እግዚአብሔር ክብር ውስጥ ለመግባት በሆነ እይታ በመለኮታዊው አገዛዝ ሥር እግዚአብሔርን የምናመልክበት እና እግዚአብሔርን የምንደሰትበት ክበብ ነው—ማቴ. 6፡13።
   ለ. መንግሥቱ እግዚአብሔር ክብሩን ይገልጥ ዘንድ ኃይሉን የሚያንቀሳቅስበት ክልል ነው—ራእ. 5፡10፣ 13።
   ሐ. የመንግሥቱ ማብራት ለአብ መክበር ነው—ማቴ. 5፡16።
4. የእግዚአብሔር መንግሥት ለመለኮታዊው አስተዳደሩ ከስልጣኑ ጋር የእግዚአብሔር በክብሩ መገለጥ ነው፤ ስለዚህ፣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እና ወደ ተገለጠው የእግዚአብሔር ክብር መግባት እንደ አንድ ነገር በተመሳሳይ ጊዜ ይከናወናሉ—ዕብ. 2፡10፤ ማቴ. 5፡20፤ 1 ተሰ. 2፡12፤ 2 ተሰ. 1፡10፤ ራእ. 21፡9-11፤ 22፡1፣ 5።
5. ፍጥረት የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲመጣ በጉጉት እየተጠባበቀ እና እየናፈቀ ነው፤ መንግሥቱ በሚገለጥበት ጊዜ፣ ፍጥረት በሙሉ ነፃ ይወጣል፣ የተገለጡት የእግዚአብሔር ልጆች ደግሞ ከከንቱነት አርነት ይወጣሉ እንዲሁም "በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ"—ማቴ. 13፡43።

*© 2020 Living Stream Ministry*